# የወያኔን የመረጃ አፈና ለመበጣጠስ አዕምሮዓችንን እናሰራ፣

# ኪሳችንን እንፈትሽ፣ ቆርጠንም እንነሳ!!!

ሰኔ 23 2002 ዓ.ም

መረጃ ኃይል ነው። መረጃ እውቀትና ሃብትም ጭምር ነው። በሃያ አንደኛው ክፍለ-ዘመን ለልማት ከሚያስፈልጉ ግብዓቶች መረጃ ቀዳሚው ሥፍራ ይዟል። መረጃን አፍኖ ትምህርትን፣ የጤና አገልግሎትን፣ ንግድን እና ሌሎችን የልማት ሥራዎችን በጥራት ማሳደግ አይቻልም። መረጃን አፍኖ መልካም አስተዳደርና ፍትህን ማስፍን የዜጎችን ዲሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶችን ማስከበር የማይታሰብ ነው። ከሁሉም በላይ ደግሞ መረጃ ማግኘት የዜጎች መብት ነው። መረጃ የማግኘት መብቱ የተገፈፈ ዜጋ መሰረታዊ የሆነ የዜግነት መብቱ ተገፏል፤ ከዚህም ጋር ስለ እራሱ የማወቅንምን ሆነ ራሱን የማሳደግ መብቱ ተነፍጓል።

መረጃን ጠቅልሎ ይዞ ለእኩይ ተግባራት ማዋል የአምባገነን ገዢዎች ሁሉ የጋራ ባህርይ ነው። መለስ ዜናዊም የአልባንያውን ኢንቨር ሆዣ ከመሳሰሉ የእውቀት ጌቶቹ በተማረው መሠረት የኢትዮጵያን ሬድዮና ቴሌቪዥን ተቆጣጥሮ ተቋማቱን ወደ ውሸት ማምረቻና ማሰራጫነት ቀይሯቸዋል።

በወያኔ ሙሉ ቁጥጥር ሥር የሚገኘው የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የሚያመርታቸውና የሚያሰራጫቸው ውሸቶች ብዛትና ዓይነት ተነግሮ አያልቅም። ቴሌቪዥኑንና ራዲዮው ዴሞክራሲና ብልጽግና በሃገሪቱ በሽብሽ እንደሆኑ ይናገራሉ። ከቴሌቭዥኑና ከሬድዮው ጣቢያዎቹ ደጃፍ ግን ዜጎች ግንባራቸው በአጋዚ ጥይት እየፈረሰ ይደፋሉ። የሚላስ የሚቀምስ ያጡ፤ ቀኑ የጨለመባቸው ወጣቶች የመከራ የጎዳና ሕይወት እዛው እደጃፍ ላይ ይገፋሉ። በቴሌቪዝኑ መስኮት ገበሬዎች ሚሊዮነሮች ሆነው ሜዳልያ ይሸለማሉ። በየገጠሩ የምግብ እርዳታ ካላገኘ ለጥቂት ቀናት ስጋውን ከነፍሱ አጣብቆ ማደር የማይችለው ዜጋ ቁጥር ወደ 15ሚሊዮን አሻቅቧል። ገዳዮች ከሳሾች ሆነው ሟቾች ወንጀለኞች ተደርገው ይቀርባሉ። ሃገረ ከሃዲዎች ሀገር ወዳዶችን በሃገር ክህደት ከሰው ወህኒ አጉረው ይታያሉ። በወያኔ እጅ የሚገኙ የመገናኛ አውታሮች የተጠደመዱት ድንጋይን ዳቦ አድርጎ በማቅረብ፣ በወንፊት ውሃ ቀዳን፣ ግመልን በመርፌ ቀዳዳ አሾለክን፣ ነጭ ኑግ ጥቁር ወተተና የዶሮ ጥርስ በመለስ ዜናዊ ቆራጥ አመራረና በወያኔ ልማታዊ መንግስት ጥረት ተመረቱ የሚል ሃፍረተቢስ ቅጥፈት በማሰራጨት ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ አማራጭ መረጃዎችን ከኢንተርኔት ድረገፆች እንዳያገኝ ወያኔ ከፍተኛ ገንዘብ እያፈሰሰ ዋና ዋናዎቹን ድረገፆች ዘግቷል። በኅትመት ሚዲያና በጋዜጠኞችም ላይ የሚደረገው አፈና ተፋፍሞ ቀጥሏል። ሰሞኑን ከተደመጡ የወያኔ ፀረ-መረጃ ሥራዎች በአሜሪካ ድምፅ ጋዜጠኛ ሄትኸር መርደክ ላይ የደረሰው ነው። ይህች ጋዜጠኛ የቱሪዝብ መስህብ ስለሆኑት ለማዳ ጅቦች ለመዘገብ ወደ ሃረር በመጓዟ እግረ መንገዷን እዚያ ያለውን ጉዳችንን ታወጣብን ይሆናል በሚል ስጋት ከአገር እንድትባበር ተደርጓል።

ይህ ሁሉ ያው የምናውቀው የአፈናና የውሸት ፍብረካ ታሪክ ነው። ወያኔ እስካለ ድረስ እየባሰ እንጂ እየቀነሰ አይሄድም። መሠረታዊው ጥያቄ “ምን ይደረግ?” የሚለው ነው።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ለዚህ ጥያቄ ያለውን ምላሽ በተደጋጋሚ ገልጿል። እንደ ግንቦት 7 እምነት በኢትዮጵያ ውስጥ ፈጣንና አዎንታዊ ለውጥ ለማምጣት የነፃ ሚዲያ መኖር ወሳኝ ነው። የወያኔን የመረጃ አፈናን መበጣጠስ ያለብን እኛው ነን። ይህን ማድረግ ደግሞ ይቻላል!!! በቅርቡ ስራውን የጀመረው የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዝን (ኢሳቴ) ይህን በተግባር አረጋግጦልናል። ኢሳቴ ሁለት ታላላቅ ጉዳዮችን አሳይቶናል -

1. የወያኔ የመረጃ አፈና ሊሰበር እንደሚቻል በተግባር አሳይቶናል። ወያኔ በኢቲቪ ላይ ከሚያፈሰው አንድ ሺህኛ እንኳን በማይሆን ወጪ ከኢቲቪ እጅግ የተሻሉ ማራኪና አስተማሪ ፕሮግራሞችን ማዘጋጀት የሚቻል መሆኑን አስመስክሯል።

2. ለሃቅ፣ ለፍትህ፣ ለነፃነት፣ ለሰብዓዊ መብቶች መከበር መቆም የቱን ያህል በሕዝብ እንደሚያስወድድ አሳይቶናል። ኢሳቱ ገና ከመነሻው የሕዝብ ቴሌቪዥን ሆኗል።

የኢሳቱ መወለድ ወያኔን በእጅጉ አስደንግጧል።ውሸት ብቻ መናገር የለመደበት ተቋም እውነትን ብቻ ከሚናገር ተቋም ጋር መፎካከር እንደማይችል ግልጽ ነው። ስለሆነም ወያኔ የሕዝብን ሃብት በማፍሰስ የሳተላይት ስርጭቶችን የሚረብሹ ሞገዶችን በውድ ዋጋ እየተከራየ ኢሳቴን ማወክ ጀመረ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ከጎኑ ቆሟልና ኢሳቴ የደረሰበትን ጥቃት የመቋቋም አቅም ገንብቶ ይመለሳል ብለን ተስፋ እናደርጋለን። መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በዚህ ረገድ ለኢሳቴ ያለውን ድጋፍ እንዲቀጥል፤ በፋይናንስ፣ በሙያ፣ በተቻለን ነገር ሁሉ ኢሳቴን እንድንደግፍ ጥሪዓችንን እናቀርባለን።

ከዚህ በተጨማሪም የወያኔን ጨኸትና ሁከት የሚቋቋም በየእለቱ የሚተላለፍ ለእውነት፣ለፍትህ፣ ለነፃነትና ለሰብዓዊ መብቶች መከበር የቆመ ሁነኛ የሕዝብ ሬድዮ ጣቢያ በአስቸኳይ መቋቋም ይኖርበታል። ለገጠሩ ሕዝባችን በአስተማማኝ ሁኔታ መድረስ ይኖርብናል። ግንቦት 7 ኢትዮጵያዊያን በዚህም ጉዳይ ላይ እንዲያስቡበት ያበረታታል።

በተመሳሳይ ሁኔታም በህትመትም ዘርፍ ወርሃዊ መጽሄትንና ሳምንታዊ ጋዜጣን ለኢትዮጵያዊያን ማድረስ የሚቻልበት ሁኔታ መፈለግ ይኖርበታል። የወያኔን የመረጃ አፍና ለመበጣጠስ የህንጻዎች ግድግዳዎችና ለመጻፊያነት የሚመቹ የሃገራችን ተራሮች፣ ኮረብታዎችና ገደሎች በቀለም መሸፈን ይኖርባቸዋል። የወያኔ ጉድ የሚያጋልጡ፣ በጎቡዕ የሚዘጋጁና የሚበተኑ በራሪ ወረቀቶች በየገበያው ቦታ፣ በየትምህርት ቤቱ እና በየቤተ አምለኮው መበተን ይኖርባቸዋል።

የወያኔን የመረጃ አፈናን መበጣጠስ እንደሚቻል ኢሳቴ ጥሩ ማስረጃ ነው። መረጃ የማግኘት መብታችንን ማንም አምባገነን ሊያፍነው እንደማይችል ለመለስ ዜናዊና ለተባባሪዎቹ በመተባበር እናሳያቸው። የነፃነት እሳት መንበልበል ይኖርበታል። ለዚህ ክቡር ዓላማ ሁላችንም አዕምሮዓችንን እናሰራ፣ ኪሳችንን እንፈትሽ፣ ቆርጠንም እንነሳ!!! !

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**